# ትግላችን ዜና


ዓለም-አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ሕብረት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board
P.O.Box 3198, 10364 Stockholm,3
SWEDEN


<u>በዚህ እትም ውስጥ፤</u>


- ርዕሰ አንቀጽ
- ዜና
- የደርግን ጋዜጦች ስናገላብጥ
- ኢትዮጵያ በአለም ጋዜጦች
- ኬነት



ቅጽ 10 ቁ. 2 ታህሣ. 1975

# ርዕሰ አንቀፅ

<u>በሞተ አይፈርዱምና</u> ...

ማንኛውም ሰው ሟች ነው ፡፡ ኃላፊ ነው ፡፡ ይህ ሞት የሚሉት ነገር "ትንሽም" "ትልቁም" አይመርጥም፡፡ሁሉንም ጊዜው ሲደርስ ይወስደዋል፡፡"በቀጠሮ ቀን" ይጠራዋል፡፡የሰዎች ሥራ ግን አይጠሩም፡፡ምናልባት አንዱ አንዱን በሚቆናቆነው አንዲጠሩ ቢደረግም፣ ድርጊቱ በቀላሉ የማይረቅ ስለሆነ ለዘላዓለም ሲታወስ ይኖራል፡፡የሰዎች ስም መነባት አንደየሥራቸው፣ለትውልዱ ትውልድ አንዳስተላለፉት የታሪክ ቅርስ ይነባልም ይወድቃልም፡፡መጥፎ የሠሩ በመጥፎ ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡መልካም የሠሩ ደግሞ፣ አይ አከሌ አንደዚህ ጥሩ ነበር፣ደግ ነበር አየተባለ በደግነቱ፣በቅንነቱ ሲወደስ ይኖራል፡፡ትላልቅ ሰዎች ደግሞ፣ማለትም ለሰው ልጅ ደህንነትም ሆነ ጥሩነት፣ ብልጽግናም ሆነ ኋላቀርነት፣ሰላም ሆነ ጦርነት የታገሉ ከዚህች ምድር ተሰናብተው "ቸሩ አገዚአብሔር" ወደአዘጋጀላቸው ዘላለማዊ ቤታቸው "ሲኦልም ሆነ ገነት" ሲወርዱ ተግባራቸው በሁለቱ ሚዛናዊ ነገሮች ሲለካ ይኖራል፡፡

በቅርብ ጊዜ ከዚህች ምድር የተለየው ብሬዥኔብም፣ ተግባሩ በእነዚህ ሁለቱ ሚዛናዊ ነገሮች ከመለካት የሚያልፍ አይደለም፡፡ብሬዥኔብ ወደሥልጣን መወጣጫ አካባቢ ቀስ በቀስ ከመድረሱ በፊት፣ የፈጸማቸው ተግባሮችና ሥልጣንን ከጨበጠ በኋላ የወሰዳቸው ድርጊቶች፣ በተግባር ሚዛን ሲለኩ አንዱ አይደሉም፡፡አንዱኛው አንዱኛውንም ከምፐንሴት የሚያደርገው አይደለም፡፡የሚጣጣምም አይደለም፡፡

ብሬዥኔብ የሥልጣንን ማማ ከመጨበጡ በፊት፣በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅት ከሶቪየት ህብረት ወዝአደሮችና ገበሬዎች፣ፓትርዮቶችና ዴሞክራቶች ጋር በነገር ቆራጥነት ፀረ–ፋሺሽት ትግል ያካሄደ ሰው ነበር፡፡በዚሁና በሌሎች ፖለቲካዊ ተግባሮቹ፣በስታሊን ዘመን ቀስ በቀስ ወደ ሥልጣን አካባቢ ሊጠጋ ችሏል፡፡ ነገር ግን ይህ መልካም ድርጊቱ፣ቆራጥነቱና ለሶቪየት ወዝአደሮችና ገበሬዎች፣ ከእነሱ ጋር ሆኖ ያበረከተው አስተዋጽዖ በተለይም ሥልጣን ከጨበጠ ወዲህ በጥቁር ነጥብ አንዲሸፈን አድርጎታል፡፡ይህ ድርጊቱ ሁለት አቅጣጫዎችን ይይዛል፡፡ አንዱኛው ፣ ምንም አንኳ አሱ የወዝ አደር ልጅ ቢሆንም፣ በሚሊዮን የሶቪየት ወዝአደሮችና ገበሬዎች ህይወት ላይ፣ባጭር አነጋገር በቢሮክራሲዝም ላይ የተከተለው ፖሊሲ ነው፡፡ ሌላው፣ የውጭው ፖለቲካው ነው ፡፡ በሀገሮች ብሔራዊ ነፃነት፣ዴሞክራሲያዊ አንቅስቃሴ ዕድገትና አረማመድ ላይ የወሰደው የወሰደው አርምጃ ነው፡፡

በሀገሩ ውስጥ በመጀመሪያ ክሩስቼብን ሥልጣን ላይ አንዲወጣ ካደረጉት ሰዎችና ክሩስቼብ በወሰዳቸው ፀረ ሶቪየት ወዝአደሮች አርምጃ የተካፈለ ነው፡፡ እሱ ሥልጣንም ከጨበጠ በኋላ የክሩስቼብን ፖሊሲ በተለየ መልክ ተከተለ አንጂ

በይዘቱ ከቀዳሚው የተለየ አልነበረም። ያም ሆነ ይህ በአጠቃላይ፣ የሶቭየት ወዝአደሮችን ጥቅም የሚፃረር፣ ቢሮክራታይዝድ የሆነ፣ ኢፌሺየንት ያልሆነ፣ ሰፊው ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ የማያደርግበት በፖሊስና በፀጥታ ጠባቂዎች የታጠረና የተሞላ መንግሥታዊ መዋቅርን አጠናከረ። ቦኋላ፣ የሶቭየት ወዝአደሮች ምርትን በብዛት እንዲያበዱጉ ከማድረጉ በስተቀር፣ምርት በጥራት እንዲመረት፣ የህዝቡ ኑሮ እንዲሻሻል፣ የሰዎች የጉልበት ሥራ በቴክኖሎጂ አቅጣጫ እንዲቃለል ያደረገው አስተዋጽኦ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ከዚህ ይልቅ ሰዎችን ማስፈራሪያ፣ የሰዎችን ሰላም የሚያደፈርሰው የሚሊታሪ ቴክኖሎጂ በፍጥነት እንዲያድግ ሆነ። ሶቭየት ህብረት በብሬዥኔቭ ዘመን በጦር መሣሪያ ሥራ ያደረገችው እርምጃ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ዛሬ ከምሳ ጉደል በዚህ መስክ ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚወዳደር፣ የተለያዩ የመርከብ ጦር ሲይስተም፣ የኒውክሌርና የሚ ሣይል መሣሪያ፣ የኬሚካልና የባዮሎጂ ጦር መሣሪያዎች፣ የኮንቬንሽናል ጦር መሣሪያዎች፣...ወዘተ...ወዘተ በማምረት ተወዳዳሪነቷን እያስመሰከረች ነው። ከዚህም የተነሳ ዛሬ በሶቭየት ህብረት ኢኮኖሚው የበለጠ ሚሊታራይዝድ ሆኗል። በዚህ ላይ እናብታና፣ ዛሬ ሁላችንንም የሚነካካን የብሔራዊ ነፃነት መደፈር ጉዳይ ላይ እናምራ።

ሶቭየት ህብረት በብሬዥኔቭ ዘመን የአንዱን ሀገር ብሔራዊ ነፃነት መድፈር የጀመረችው፣ የህዝብን ዲሞክራሲያዊ መብት መገፈፍና መርገጥ የጀመረችው በኢትዮጵያችን አይደለም። ይህንንም ዱፍረት የተሞላበት ፖሊሲ፣ ፖሊሲ እንበለውና፣ የምትከተለው እንደየበታው ርቀትና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ይለያያል። በመጀመሪያ ጊዜ ሶቭየት ህብረት የአንዱን ህዝብ በንቀትና በዱፍረት በመመልከት ያካሄደችው የማን አለብኝ ወረራ በመጀመሪያ በሀንጋሪ በ1956—በክሩስቼቭ ዘመን ቀጥሎም በ1968 በቼኮዝሎቫኪያ ላይ ነበር። ይህ የፕራግ ጥቢ የተባለውን እንቅስቃሴ ለማፋፈን የወሰደችው እጅግ ጀብደኛ አርምጃ "ቀይ ጦር ሠራዊት" ተንጋግቶ በመግባት የብዙ ሰዎችን ደም እንደጉርፍ ያፈሰሰችበት ወቅት ነው። "ሶሻሊዝምን በታንክ ለመከላከል" የተደረገው ወረራ ምን ያህል ፀረ ሶሻሊዝም አዝማሚያ እንፃስሩ መገመት ከባድ አይሆንም። ይህ በተለይም በምሥራቅ አውሮፓ ውስጥ የምትከተለው ፖሊሲ፣ብሬዥኔቭ እራሱ የተሰየመው "የተገደበ ብሔራዊ ነፃነት" /Limited Souvernity) ከሚለው ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። ይህም ማለት እነዚህ አገሮች የራሳቸውን የውስጥም ሆነ የውጭ ፖለቲካ እንደፈለጋቸው ሊተልሙ ና ሊከተሉ አይችሉም። ይህንን ከማድረጋቸው በፊት "በህጉ መሠረት" ሶቭየት ህብረትን ማማከር አለባቸው። "የሶሻሊስት ፖሊሲ"ን በተጨማሪ በፖላንድ ውስጥ በ1970 ዎቹ በቀጥታ ወረራ ባይሆንም



የወዝአደሩን እንቅስቃሴ ለማፋፈን ያደረገችው ተፅዕኖ የተለያዩ የፖላንድ መሪዎች የብዙ ወዝአደሮችን ደም እንዲያፈሱ አስደርጋለች። "ሶሻሊዝም ካለወዝአደሩ [illegible]" ሌላው በቀርበ ጊዜ በአፍጋኒስታን ላይ ያደረገችው አይን ያወጣ ወረራ ነው።

ከዚህ ወዲህ ግን ዛሬ ሶስተኛው ዓለም በሚባል የሚታወቁ ሀገሮች ላይ የምትከተለችው የምትከተለው ፖሊሲ ነው። ይህ ፖሊሲ በቀጥታ ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ከምታደርገው የስፈር እና ኢንፍሉየንስ ውድድር ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። ለዚህ ዐነዋ የተለየና እራሱን የቻለ ቦታ በክሩስቼቭ ጀማሪነት በብሬዥኔቭ ተግባራዊ አቅራጊነት ወጥቶ ዛሬ በብዙ የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች የሚቀየስ ፖሊሲ ነው። ፖሊሲው ላይ ላዩን ሲያዩት እንደማር ጣፋጭ ሲፍቶትና ሲቀምሱት ግን እንደሬት የመረረ ነው። ይህም ፖሊሲ፣ ከቀኝ ወይም ከእጅ አዙር ቀኝ ቀኝ አገዛዝ ሥር "የተላቀቁ" የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች የካፒታሊስት አለባን እ ንገት በመከተል ሶሻሊዝምን መመሥረት ይችላሉ፣ እንዲሁም በጥቅሉ የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች የሶቭየት ህብረት የተፈጥሮ ጓደኛ /natural alloy/ ናቸው የሚለው ሃሳዊ መሰል ፖለቲካ ነው። በኩባ፣ በቬትናም፣ በቬትናም ተመሪነት በካምፑቼያና በላኦስ የምትከተለው ፖሊሲ፣ በአፍሪካ፦ በአንጎላ፣ በሞዛምቢክ፣ በኢትዮጵያችን በአረብ አገር፦ በደቡብ የመን ገብታ የህዝቦችን ብሔራዊ ነፃነት በመገፈፍ የምታራምደው ፀረ ህዝብ ፖሊሲ፣ በእነዚህ ሀገሮች ያሉ ህዝቦች ብሔራዊ ነፃነታቸው ከመገፈፉ አልፎ ህዝቦች በእርስ በርስ ጦርነት እንዲፋጁ፣ ያሉት መለስተኛ ቅራኔዎች ተባብሰው ህዝቦች በመታገር እንዲኖሩ የምታደርገው ድርጊት ቀን ተቀን ህዝቦቹ ወደስቃይ አፋፍ ላይ ቢጥል፣ በሶሻሊዝም ላይ ያላቸው እምነትና ፍላጎት በዚያው መጠን እየጠፋ እንዲሄድ አድርጋለች።

ወደሀገራችን ላይ ብቻ ብናተኩር፣በቅርቡ ከምንበማው፣ ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችን፣አባቶቻችንና እናቶቻችን ቀን ተቀን ከሚቀምሱት ጦርነትና ችግር፣ አለመተማመንና መፈራራት በነነበ፣ሶቭየት ህብረት ሀገራችን ገብታ የፈጸመችው በደል የሀገራችንን እድገት በያንስ ለአሥር ዓመታት ያህል ወደኋላ እንዲገፋ አድርጋለች። የ20 ዓመት "የወንድማማችነት ውል" ተብሎ የተፈረመው ሁለተኛው፣ዲወጪሉ ውል /የባርነት ውል/ ውጤቱ ዛሬ ቢታይ እኛ ተገዢዎች እነሱ ገዢዎች፣እነሱ ዘራፊዎች እኛ ተበዝባዦች፣ ሀገራችን የነሱ የጦርመሣሪያ መለማመጃ፣የጦርነት አውድማ የወንድማማቾች የእርስ በርስ ማጫረሻ ሆናለች። ከዚህም የተነሳ፣ ዛሬ ሶቭየት ህብረትን ባር ቀጠሎ ባይቀር ጫፍ ላይ ወዱቀ እንደሚከረፋ ሥጋ ይጠላታል። ሶቭየት ህብረት በብሬዥኔቭ ዘመን በሌሎች ሀገሮችና በሀገራችን ገብታ ያተረፈችው ውጤት መጠላትን መናቅን እንጂ ሌላ አይደለም።

በእርግጥ ይህ ሁሉ የአንዱ ሰው ፖለቲካ ብቻ አይደለም። በስተጀርባው ብዙ ሰዎች አሉበት። ሆኖም ግን የአንዱ ሀገር መሪ እንደሀገሩ ሀገ መንግሥት በውጪም ሆነ በውስጥ ፖለቲካው ወሳኝ ቦታ አለው። በዚህም ብሬዥኔብ በተከተላቸው ፖለቲካዎች ወሳኝ ሚናዎችን ተጫውቷል። በዘመኑ የተከተላቸው ፖለቲካዎች ሲያስመሰግኑትና ሲያስወቅሱት የሚኖሩ አይደሉም። በጥቅሉ ነጥቦች የተሸፈኑ ናቸው። "የሞተን ሰው ከመቃብር ውስጥ መፍረድ አይሁንብን እንጂ"።

እንደተለመደው አዲስ መሪ የብሬዥኔብን ቦታ ወስዷል። ይህ ሰው ዩሪ አንድሮፖፍ ይባላል። አዲስ መሪ ቦታውን መውሰዱ፣ አዳዲስ ሰዎች ፖሊት ቢሮ ውስጥ መግባት በመሠረቱ የሶቪየትን ፖሊሲ አይቀይረውም። አዲሱ መሪ ዩሪ አንድሮፖፍ እንዳለው፣ የብሬዥኔብ ፖሊሲ መመሪያው ይሆናል። ይህ አፋዊ ብቻ ባይሆን፣ ከሶቪየት ህብረት የርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካ ሁኔታና ዓለምን ለመቆጣጠር ካላት ፍላጎት ጋር በጥብቅ የተያያዘ በመሆኑ ተግባራዊ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። እኛም የጀመርነውን የነፃነት ትግል በመተባበርና እጅ ለእጅ በመያያዝ ግንባራችንን በናጥፍ መቀጠል አለብን።

-///-     -///-     -///-     -///-



ዜና

የተባበሩት ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች አንድነት ማህበር በሰሜን አሜሪካ 7ኛውን ዓመት ጠ/ጉባዔ ከነሐሴ 1-4 /1982 ቺካጎን ተን በሚገኘው ሎዮላ ዩኒቨርሲቲ ሲያካሂዱ፣ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ደግሞ 22ኛውን ጠ/ጉባዔውን ከነሐሴ 2-5 /1982 በቤልጅግ አገር በብሩሴል ከተማ አካሂዷል። ሁለቱ እህት ማህበራት ከተመሠረቱ ጀምሮ ብዙ ፈተናዎችን ያዩና የተጋሩ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለብሔር/ለብሔረሰቦች እኩልነት፣ ለብሔራዊ ነፃነት በሚደረገው ትግሉ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ጎን በመሰለፍ አያሌ አስተዋጽኦችን ያበረከቱ ተራማጅ ድርጅቶች ናቸው። ዛሬም ከዚህ የፀና አቋማቸው ወደኋላ ባያፈገፍጉ ለረጅም የነፃነት ትግል ታሪካቸውን ሲያዩ ለኢትዮጵያ ተራማጆች፣ ዴሞክራቶችና ሀገር ወዳዶች ትልቅ የሞራል ግሥት እንደሚሰጡ አያጠራጥርም።

ሁለቱ እህት ማህበራት በጉባዔያቸው መጨረሻ፣ በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ ላይ አብዮታዊ የፖለቲካ ውሳኔ በማሳለፍ፣ የዛሬው እንገብጋቢ ጥያቄና አጣዳፊ ተግባር የጋራ ግምባር መመሥረት መሆኑን አጥብቀው አውስተዋል። በዚህ የጋራ ግምባር በሚለው የውሳኔአቸው አንደኛው ክፍል ውስጥ፣ ሁለቱም ማህበራት፣ የዛሬው የኢትዮጵያ ህዝቦች ቀንደኛ ጠላቶች፣ የወታደሩ አምባገነን መንግሥትና ቢሮክራሲው እንዲሁም እነዚህን አቅፈው ደግፈው የሚያንቀሳቅሱት የሶቪየት ህብረትና ግብረአበሮቿ መሆናቸውን በማያሻማ ሁኔታ አስቀምጠዋል።

የተባበሩት ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች አንድነት ማህበር በሰሜን አሜሪካ፣ የህዝባዊ ግምባሩን መቋቋም ጠቃሚነትና የሚኖረውን ባይኮሎጂካል አምጻት በውሳኔው ውስጥ እንደሚከተለው ያሰፍራል።

"ሰፊ መሠረት ያለው ህዝባዊ ግንባር መቋቋም፣ ዛሬ አንዱ አየሩመ፣ ሌላ ጊዜ እየጋመ በዱር በገደሉ፣ በየፋብሪካው፣ በየጦር ሰፈሩ ለሚካሄደው ትግል አዲስና ከፍተኛ ኃይል ይሰጠዋል። የኢትዮጵያ አብዮት ተስፋ ሳይቆረጥ፣ የመደራጀትና የመታገል ፍላጎት ያለው የርስ በርሱ ትርምስ ሳስበረገገው፣ ውስጥ ውስጡን እየተሰገመገመ ጊዜ ለሚጠብቀው የህዝብ ብሶት፣ እንዲፈነዳና ዜዳር አስከዳር እንዲቀጣጠል ይረዳዋል"። በመቀጠል፣

"ዛሬ ባለንበት ሁኔታ ሰፊ ህዝባዊ ግንባር መመሥረት አዲስ የተስፋ ብርሃን ይፈነጥቃል። የርስ በርስ ጭፍጨፋው፣ የርስ በርስ ጦርነቱ ማከተሚያ መቃረቡን፣

ከአምባገነኑ ወታደራዊ አገዛዝ ባሻገር፣ የዴሞክራሲ፣ የእኩልነት፣የሰላምና የብልጽግና ጎዳናው አሩቅ አለመሆኑን ለኢትዮጵያ ህዝቦች ያበስራል፡፡በዚህም የላሸቀው ወኔ፣ የወደቀው ሞራል፣ የሻከረው የወንድማማችነትና የእህትማማችነት መንፈስ ይታደሳል፡፡ በዚህ ሁኔታ በትግል የሚነሳውን ህዝባዊ ኃይል እንኳን ባንዴ አገሩ ማማ ተደገፍ የቆመ ወታደራዊ መንግሥት፣ ምንም አይነት ምድራዊ ኃይል አይገታውም"፡፡ /የፖለቲካ ወብኒ ገጽ 16 አንቀጽ 2ና3/ በማለት የኢትዮጵያ ህዝቦች ዕድል በዚህ የጋራ ግምባር መሠረት ላይ የተንጠለጠለ መሆኑን አጥብቆ ያወሳል፡፡

እንደዚሁም በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በውሳኔው ውስጥ የጋራ ግምባሩን አስፈላጊነት እንደሚከተለው ያስቀምጣል፡፡

"ህዝቦች በወንድማማችነትና በፍቅር የሚኖሩባት፣ ብሔራዊ ነፃነቷን የማታስደፍር፣ በሰላም የበለፀገች ህዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት የሚወሰነው በዚህ በተባበረ ጠንካራ ተራማጅና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ሰፊ ግምባር ህልውና ማግኘትና ያለማግኘት ነው"፡፡ በማለት የግምባሩን መመሥረቱ አስፈላጊነት አያወሳ፣ ይህ ግምባር የትኞችን ኃይሎች እንደሚያቅፍና ምን ዓይነት መልክ መያዝ እንዳለበት ቀጠል ብሎ ያብራራል፡፡

" በኢትዮጵያ መሠረት ያለበት የተባበረ የትግል ግምባር፣ በጥቂት መኮንኖች የሚመራውን ፀረ ህዝብ ትምክህተኛ አረመኔያዊ አገዛዝ፣ቢሮክራቲውን፣ የሶሺየት ተስፋፊ መንግሥትና ግብረአበሮቹን በዋነኛ ተቀዳሚ ጠላት የሚያስቀምጥ፣ እነዚህን የሚታገሉ መደቦች፣የህብረተሰብ ክፍሎችና የብሔራዊ ነፃነታቸው መደፈር የሚያስቆጣቸው አገር ወዳድ ዜጎችን የሚያሰባስብ መሆን አለበት፡፡ የሚፈጠረውም ግምባር አጭርና የረጅም ጊዜ ፕሮግራም ኖሮት ሰፊ ኃይሎችን ሊሰበስብና ሊያሰባስብ የሚችል መሆን አለበት" ፡፡በማለት የግምባሩ አጠቃላይ ይዘት ይህንን መምሰል እንዳለበት ያመለክታል፡፡



ሠርቶአደርገና የዛሬይቱን ስናገባበት

ረቡዕ ሰኔ 9 ቀን 1974 የወጣው ሠርቶአደር [illegible] የኢሠፓአኮ ጋዜጣ አድልዎንና ጉቦን አስመልክቶ ስለተ[illegible] "የብሔራዊ ቁጥጥር ኮሚቴ" እንዲህ በማለት ያብራራል፡፡

"ብሔራዊ ቁጥጥር ኮሚቴ" በሶሻሊስት አገሮች የሥራ ጉብኝት ያደርጋል ይለናል፣ በመቀጠል — ስለህዝባዊ ቁጥጥር ዓላማ ከወታቀርና አሠራር የረጅም ጊዜ ልምድ ካካበቱት የሶሻሊስት አገሮች ልምድ ለመቅሰምና ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አዛምዶ ለመሥራት የሚቻልበትን ሁኔታ ለማጥናት "የብሔራዊ ቁጥጥር ኮሚቴ" ዛሬ ወደ ምሥራቅ በርሊን ይሄዳል በማለት ...የሚሄዱበትም አገሮች ፣ ጀርመን ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ ሶሺየት ህብረት፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ሀንጋሪና ሩማንያ ናቸው ብሎ በዝርዝር ይገልጻል፡፡

ይገርማል "ልጅ ከአባቱ ይማራል"እንዲሉ፡፡ እውነትም የረጅም ጊዜ ልምድ ካካበቱት ትምህርት ለመቅሰም/ ጉቦንና አድልዎን በማመልከት፣ በዘመዱ አዝማዱ መጀጀምን፣ በሥልጣን መባለግን ፣ በዚህ መስክ እንደምሥራቅ አውሮፓ የተካነ የለም፡፡ ጉቦና አድልዎ፣ በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች የቢሮክራሲው ማንቀሳቀሻ የሆነ ለመሆኑ በገሀድ የሚታወቅ ነው፡፡ ሌላው ቢቀር፣ ከአንዱ የትምህርት ቤት ዲሬክተር ብንጀምር፣ ለባልየው አንዱ ነገር ለስጦታ ቢቀርብ፣ ለሚስትየው ሻንጣና ሽቶ ተያይዘው ይቀርባሉ፡፡ ማርክሲዝምና ሌኒኒዝምን "እንከበክባለን"የሚሉት ፕሮፌሰሮች እንኳ በጠርሙስ ውስኪ የሚደለሉበት ጊዜ ጥቂት አይደለም፡፡ ይህንን ምሥራቅ አውሮፓ የተማሩ ይበልጥ ያውቁታል፡፡ይህም ከፊዩዳል ህብረተሰብ ያላነሰ የተገማማ አድልዎና ጉቦ እንደሆነ፣ ሥር የሰደደ ለመሆኑ፣በዚህም የረጅም ጊዜ ልምድ እንዳላቸው ዓለም ያውቀዋል፡፡የኛም ጉዶች ወደነዚህ አገሮች የሄዱት በይበልጥ እንዴት ጉቦ መብላት የሚቻልበትን አድልዎ የሚደረግበትን ዘዴ ለማጥናት ወይንስ እውነተኛ ቁጥጥር ለመቅሰም? ሌባ ከሌባ ምን ይማራል ? ያው ሌብነትን ነው፡፡ ያውም የረቀቀ አሠራረቅን!!

—//—

ግንቦት 21 1974 በወጣው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ላይ "ከጊዜ ሊቀ መንበር" ንግግር በሚለው የመሪ ቃል ስር የሚከተለው ሠፍሯል፡፡

"ለአንድ ህዝብ ህልውናው ታውቆለት በእውነተኛ ነፃነት ከመኖር የበለጠ ክቡር ነገር የለም፡፡ የዓለም ህዝቦች ሁሉ የዘመናት ያልተቋረጠ ተጋድሎ የመ

ወረሻ ገብ ይኸው ነው:: የኢትዮጵያ በሬህዝብ የትግል ዝዝም ከዚህ ውጪ የሚታይ አይደለም" ይላል::

ወይ ሊቀ መንበር/ አንዳንድ ጊዜ እንደቀድሞስ ለመናገር ይቃጣቸዋል:: ትዝ ሲላቸው ለካስ በሌላ ዓለም ውስጥ ናቸውና፣ ከእንቅልፋቸው እንደነቃ ሰው ብንን ይሉና ምን ነበር የተናገርኩት ወደማለት ያመራሉ::

"ጓዱ ሊቀመንበር" እርስዎ ከልብዎ አይደለም የተናገሩት እንጂ፣በ እርግጥም ለአንድ ህዝብ ህልውናው ታውቆለት በእውነተኛ ነፃነት ከመኖር የበለጠ ክቡር ነገር የለም:: ይሁንና ግን ፣ለርስዎ ምናልባት ይህ የተናገሩት "እውነተኛ ነፃነት" በእርስዎና በገበረአበሮችዎ አምባገነንነትና ፈላጭ ቆራጭነት የተተካው፣ህዝባችንን አረመኔአዊ በሆነ አፈናር ውስጥ የከተተው መሆኑን አ.ተገነዘቡትም? ህዝባችን እርስዎንና ገበረአበሮችዎን አይኔ ላአፈር እያለ በመማፀን ላይ እንዳለ አልተረዱትምን? እርስዎ የተናገሩት እውነተኛ ነፃነት በርስዎና በገበረአበሮችዎ መቃብር ላይ ብቻ የሚመሠረት መሆኑን ከምን ጊዜውም ይበልጥ አልተገነዘቡትምን? ምናልባት "አምላክ በተአምሩ"ዕዱሚያን በጥቶት ወይንም "ከቢልል ውስጥ ጉትቶ አውጥቶት" የኢትዮጵያን ህዝቦች እውነተኛ ነፃነት ያስይያት ይሆናል ::"ለዚያው ያብቃያት"

//-//

## ርም ለገበያ

ባለፈው ሐምሌ ወር 1982፣ የኮሎኔል ፍስሐ ደስታ ባለቤት በኢትዮጵያ አየር መንገድ በአንደኛ ማዕረግ ተሳፍረው ወደሮም ለገበያ ይጓዛሉ:: አባቸውን "ከአደጋ ለመጠበቅ"እያሉ የጸጥታ ጠባቂዎች በአንድ በኩል ብዙ ሰው የማይመሳሰስበትን አይሮፕላናችንን ቦታ እንዲያጣበቡ ሲደረግ፣በሌላ በኩል ለመጸዳዳት አልፍ አሬፍ የሚንቀባቀበውን ተሳፋሪ በጥርጣሬ አስጨንቀውት ነበር::

አውሮፕላኑም ሮም ደርሶ ተሳፋሪው ሲወርድ ሮም ያሉት የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሠራተኞች የአውሮፕላኑ ማረፊያ ፊት ለፊት ያለው በር ጋ ይጠባበቁ ኑሮ ወይዘሮን ከነሴኪዩሪታቸው ሊቀበሏቸው ጠጋ ይላሉ:: በዚህን ጊዜ የሴኪዩሪቲው ጓዱ ጋሳፈ በመቆጣት፣ " መኪና እዚህ ድረስ ይዛችሁ ለምንድን ነምንድነው ያልመጣችሁት? ለመሆኑ ፕሮቶኮልም አታከብሩም ማለት ነው" ? በማ



ለት ቡራ ከረዩን ይለቀቃል:: ይህን ዱንፋታ ያዩ ተመልካቶች ይገርማቸውና " የአንድ አገር መሪ እንኳ ቢመጣ መኪና ከቆመበት ድረስ በእግሩ ነው የሚሄደው" ይላሉ :: አንዱ "ይህ ምን ያስደንቃል" የደሴን ሚስቶች ወደአውሮፓ ለገበያ በመጡ ቁጥር አውሮፕላኑ ሞልቷል እየተባለ እነሱኑ ማመላለሻ ብቻ ሆኗል" በማለት ምሬቱን ይገልፃል:: በዚህ ድርጊት ከአውሮፕላኑ የወረደው ሌላው ህዝብ ቆሽቶ እያረረና ከንፈሩን እየመጠጠ ወደየአቅጣጫው ይበታተናል:: ወይዘሮም በፀጥታ ጠባቂያቸው ታጅበው ወደ ተዘጋጀላቸው መኪና ጋ ይጓዛሉ::

አገባቢ አነኮለኔልና ሚስቶቻቸው ለቅንጦት ገበያ ወደ ፈረንጅ አገር ሲመጡ ስንትና ስንት ሺህ ዶላር ይዘው እንደሚመጡ ለአንተው እንተዋለን :: መቼም ሥራቸው "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል"እንዳለቸው አህያ ሆኗል::

-//-

## ከገጽ16 የዞረ

በ 28.10.82 የታተመው ታገስ ስፒገል የተባለው ጋዜጣ የሚቀጥለውን አሥፍሯል::" አንድ የቲፒልፍ/TPLF / ቃል አቀባይ ካርቱም ላይ በሰጠው ቃል መሠረት፣ አንዱ የነፃ አውጭው ቡድን አዲ ዲጓዱ በሚባል አካባቢ በአንድ የኢትዮጵያ ሚሊታሪ ኮንቦይ ላይ ጥቃት አድርሷል::በዚህም ጥቃት 100 የሚሆኑ የመንግሥት ወታደሮች የሞት ወይም የመቁሰል አደጋ ሲደርስባቸው፣ 112 ወታደሮችና 35 ሲቪሎች ተማርከዋል::ይህንንም ድርጊት ለመበቀል ሲል ከሁለት ቀናት በኋላ የመንግሥት ወታደሮች ደርሰው ሁለት ቤቶችና ሰባት ህፃናት ገድለው ዘጠኝ ቤቶችን አቃጥለዋል::

-//- -///-

## ሥልጣኔና ኃላ ቀርነት፣ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት፣ ጭካኔና አረመኔነት::

አብዛኛውን ጊዜ ብዙ ተረቶች ምሳሌዎች፣አነጋገርና ስልቶች፣የታሪክ
ጠባያትና መጣጥፎች፣እንዳንዴም ውስጠ ወይራ፣ሰምና ወርቅ እንዲሁም አበ
ባሎች ከየትም ከየትም አርጌ ሆነው ይሁኑ አዲስ፣ተሸሽለው ይሁኑ ተጠመው
ብቅ ቢሉ፣ ይህማ የአባቸው የአለቃ ገብረሐና ናት ተብሎ ይደመጣል::በሚ
ውም ከት ከት ብሎ ከሳቀና ከአፃመጠ፣አፍይ ብሎ አይኑን ከጠረገ፣ከተረጋጋ
በኋላ ብዙ የተረሱ ነገሮች ከሳቅ ጋር ተደባልቀውበት ትዝ ይሉትና ታሪክ
ታሪኩን ጠርቶት ጠባያ በጠባያ እስከእኩለሌሊት ድረስ እየተጓተተ ከዚያም
ወሬው እንደዚህ ጭራ አያወጣ፣ እየደረ እንደሚሄዱ ማንም የአቋቺ ዝጠቆች
የሚያውቀው ነው::

ገብረሐና የሚል ስም፣ ሥራና ጉዱ ቢነበ ደግሞ የባለቤታቸው የወይዘ
ሮ ማዘንጊያ ስም አልፎ አልፎ አንዳንዴ አለቃን ቢያታሉ፣ በአለቃ ቢታለሉ
ቢሸደቡ፣ቢሸደቡ፣ቢቀኑ ቢያስቀኑ፣ቢቀለድባቸውና በአለቃ ቢቀልዱ ሁላችንም
ሳንሰማ አልቀረንም::የቤቶች አኩልነት ?

ለእኛ ፊክ ኤዲህ ሲባል ቁዝር ያሉ ደንደባም ፊውጻል በአይናችን ላይ
ውር ቢል እንደሚታየን፣አለቃም ገብረሐና ሲባሉም አንዱ አጠር ቀጠን ያሉ ሸ
በቶና ነጭ ጭም የለበሰ ፊት ያላቸው፣የራስ ቅላቸው በጥምጥም የተሸፈነ መስ
ቀል መያዣያ፣ጭራና በቃሉ የማይለያቸው ቀልደኛ፣ደስተኛ፣ፈገግታ ሁሌ የማይለ
ያቸው አዉ ፖች ዝጠቆች ፍጡር ትዝ ይሉናል::

ወይዘሮ ማዘንጊያ የሚባሉ ስም ስንሰማ ደግሞ፣ረዥም ትከሻቸው ሰፋ ያለ
ከአርባ ዓመት አጋማሽ ላይ ያሉ ጠንካራ እናትነትም እመቤትነትም ሠራተኝነትም
ጠባዮችን አጣጥደው የያዙ ቤት ወይዘሮ በተለይማ ጠጕሯን ወደላይ ጠቀልላ ት
ንሽ ሻሽ ጣል አድርጋ የምትውረገረገዋን ቢኖራ ቦሬያን ይመስሉናል:: /ምንና
ምን ትሉ ይሆናል/ የቦሬያ ሱሬን ቀመና ትከሻ፣ ተረከዝና አረማመዱ፣ገልምጧና
አስተያየት እንዴያው ከወይዘሮ ማዘንጊያ ጋር እናነጻለን::ለምን?ፈጽም አይ
ገባንም::ምናልባት በልጅነታችን በአእምሮአችን የተቀረጸ ሥዕል ይሆናል::እንተ
ዋውና:-



ቦሬያ ሱሬን ዕድሜዋ አርባ አምስት አመት፣ ሙያ የፊልም ተዋናይ፣የሁለት
ልጆች እናት፣ የኢጣሊያዊ ተወላጅ፣ ተቀማጭነቷ በአሜሪካንና በአውሮፓ ትላልቅ ከ
ተማዎች፣...
እንደሚባለው የከስ ዶሴዋ እንደሚገልጸው በአለፉት አመታት የገቢ ቀረጥ ለመንግ
ሥት በአለማስገባትዋ በአገር ውስጥ የገቢ መሥሪያ ቤት አማካኝነት ተከሣ ነበር::
በኢጣሊያን አገር ውስጥ በአለመገኘትዋና ቀረጥም በጊዜው በአለመክፈልዋ አቃቤ ህ
ጉ ደጋግሞ የእሥራት ማዘዣ አባልፍባት ነበር::
ከዚህም የተነሣ እኛ ልናጣራ በአልቻልንበት ምክንያት ወይዘሮ ቦሬያ ሱሬን በድን
ገት ይሁን በአጋጣሚ ወደኢጣሊያን ስትመለስ አይሮፕላን ጣቢያ ላይ ትያዛለች::
ካስቴራ በተባለውም እሥር ቤት ለአንድ ወር ጊዜ ያህል በእሥራት ታባልፋለች::
ከእሥር ቤትም እንደወጣች የኢጣልያን እሥር ቤት ሁኔታ እንዲሻሻል ለመታገል ቆር
ጣ መነሳትዋን በተፈታች በሳምንቱ ጋዜጣዊ መግለጫ ከዚህ እንደሚቀጥለው ሰጠች::
ቢኖራ ሱሬን የቤት ጠበቃዋን ይዛ ጠጕር አስተካካዮዋንና አልባሽዋን አስከትላ እሥር
ቤት ውስጥ የለከፉትን የመንፈስ ጭንቀት በሁለት የሳይኮ ቴራፒ ንግግሮች ከጠገነች
በኋላ፣ "የደረሰባትን ገፍና በደል"ለተጋበዙት ጋዜጠኞች እንዲህ ብላ ትዘምራለች::
በእሥር ቤት አለች፣"በእሥር ቤት ውስጥ አንድ ኪሎ ሰባት መቶ አምሣ ግራም ክብደት
እንደምታዩኝ ቀነስኩኝ፣..." ድምጸዋን አለሥልባ ረጋ ብላ በእመቤት አነጋገር ቃላ
ቶችን እየቀጠረች "የማይረባ አባዝኛና አስቃቂ ታሪክ የሚዘምረው ከአይሮፕላን ጣቢያ
ነው::በመጀመሪያ ፍተገራፍ አንሺዎች ከአለእኔ ፈቃድ በቂ ፍተገራፍ እንዲያነሱ ይደረ
ጋል:: ይህ የሚያበሳጭና የሚያደክም ነበር:: አሁንም ፍተገራፍ አንሺዎች እኔን ብዙ
ባያነሱ መልካም ነው:: በካስቴራ እሥር ቤት ውስጥ አንድ ክፍል ብቻ ይሰጠኛል:: ይ
ህም የእሥራት ጊዜዋን የአባለፍኩበት ቀፍ ነበር:: ስለዚህ ክፍል ባጫውታችሁ ለዛ የ
ሌለው አመዳም፣ገሬጭ በቀጡ በጥንታዊ የባሱን ቤት ቦኑያች፣ጠረጴዛዎች የአልተዘጋጀና
አስፈላጊ ምንጣፍ፣ የግድግዳ ትላልቅ ሥዕሎች፣ ትምቧጭንና ቁባቁቦች የጎደሉት ደባባ
ጉጀ በአእምሮአችሁ እንደሚታያችሁ ተስፋ አደርጋለሁ:: እዚያ ካስቴራ በተባለው መን
ደር ውስጥ የአለው ጭቆና ሰብአዊ መብት መረገጥ ይህ ነው ተብሎ የሚነገር አይደለም
ለሳው ቀርቶ በቀን የፀሐይ ብርሃን እንዳይ ከእሥር ቤቱ ክፍሉ እንድወጣ አይፈቀድል
ኝም፤፤ገምቱት በእነዚህ አራት ሳምንት ጊዜ ውስጥ አንድም የፊልም ሆነ የቲያትር መከ
ፈቻ ሥነ ሥርዓት ምሽት ላይ እንዳልካፈል፣እንግዶችን ተቀብዬ እንዳነጋገር፣ ትላልቅ የ
ገበያ ምሽቶች ላይ እንዳልገኝ ፈጽሞ ታግጄ ነበር::

በዚህ ገላጻዊ ደቂቃዎች ለስላሳና ደካማ ርህሩ ልብ የአሳቸው የተጋበዙ አዳማጮች በቀስታ መሐረባቸውን ከኪሣቸውና ከቦርሳቸው አያወጡ አይናቸውን ያባብሱ ጀመር:: ወይዘሮ ሉሬን ግን ልብዋን አደንዱና ምራቅዋን ውጣ መገለጫዋን ትቀጥላለች :: "አሥር ቤቶ አንድ ቀያይ ብቻ ነው የአለው:: አሁንም ለትንሽዋ ሁሉ ለማትለየኝ ውሻዬ ከፍሌ ዱረስ መጥተ ምግብዋን እንዳያዘጋጁላት ተከልክሎ ነበር:: የአሥር ቤቶ ምግብ አዳራሽም የምግብ አይነቶች ማማረጫ ደብተር የአለው ይመስላችኋል? አንዱም የምግብ አይነት መገለጫ ካርድም የላቸውም:: ከዚህ የተነሳ ምግቡን ከውጭ ከሌላ ትላልቅ ሆቴሎች እንድመጣልኝ የግድ ማስደረግ ነበረብኝ:: ከውጭ የሚመጣልኝ የሆቴል ምግብ ደህና ቢሆንም የሚያሳዝነው ግን ከሆቴል በ^ እስከ አሥር ቤቶ ከፍሌ ዱረስ መንገዱ ራቅ ያለ በመሆኑ ምግቡ ሁል ጊዜ ቀዝ ቀዝ ብሉ ነው የሚደርሰው:: ለሆዬ የሚስማማ አልነበረም::እንደምታውቁት በማንኛውም አጭር የህይወት ታሪኬ ላይ ቢሆን ለማንበብ እንደምትችሉት፣እኔ የትኩስ ምግብን በጣም የምወዱና ትኩስ ምግብ ብቻ የምበላ ሴት ወይዘሮ ነኝ":: አድማጮችና አስተዛዛኞች ችግር ተካፋዮች ከነፈራቸውን ሲመጡ፣እና ንጧቸውን ሲጠርጉ፣ ከተቀመጡበት በሀዘን ሲገላበጡ፣

"በጋዜጣ፣በሬዲዮ፣በቴሌቭዥን፣በመጽሔቶች ስለእኔ ቀን በቀን ባይጻፍ፣ባይነገር፣ባይታይ ኖሮ ዛሬ እዚህ ቁጭ ብዬ ብዬ መናገሬ የሚያጠራጥር ነበር::ምናልባትም ገና ዱሮ ሞቼ ነበር"::አሁን ግን አለቻ ሁለት እጆችዋን አንስታ"እሁን ግን እኔ አንዱ መጽሐፍ በመጻፍ ኢጣሊያኖች አይናቸውን እንዲከፍቱ አደርጋለሁ:: እርእስቱ የካስተራ ቢስል ይባላል:: በአሥራ ሦስት ቋንቋ የመተርጎም ኃሳፊነትና መብት ለአሳቸውና ለሚመለከተው ከፍሎች እንደተሸጠም በዚህ አጋጣሚ አገልጽላችኋለሁ::ይህ ታሪክ ደገም በእርግጥ በሆሊውድ ውስጥ ፊልም እንዲነሳ ይደረጋል:: ገዱ የለም ከበብ ተዋናይነትን እኔው ራሴ አጨውታለሁኝ::ፒተር ኡስቲኖቭ የአሥር ቤቶ ነፍስ አባታችን፣ ቄስ ማን ነው ስማቸው? ተውት ዋናው ነገር አባቸውን ሆኖ ይጫወታል:: እንደዚህ አድርጌ ስለአሥር ቤታችን ሁኔታ የአገሬ ህዝብ እንዲያውቀው አደርጋለሁ::ዕውነቱን አፍረጥርጨ አጋልጣለሁ::ህዝብ ይወቀ ምን ይመጣል በላቹሁ ነው? አረአስቴ/ ባፋን ኩሉ ቡታና/ ብላ እንደተቀጠች አንዱ ጋዜጠኛ ባይታሰብ እንደጥይት በመተኮስ ብዱን ብሉ ቢኖሬ/ቢኖሬ በጣም ይቀርታ ቢኖሬ የተናገሩት በጣም የሚያሳዝን ነው::ለመሆኑ ግን አብዛኛው እሥረኛ 30 ቀን ብቻ ባይሆን 30 ዓመት፣መንቀሳቀስ ባይሆን በአንዱ ከፍል አገር ተወሮች ተጠፍረው እንደሚቀመጡ፣ ለውሻ ባይሆን ለራሱ የሚመገበው ምግብ እንደማይቀመው



ከአርቡ ሁኔታ በተለየ አስቃቂና አሳዛኝ የመከራ ዘመን በአሥር ቤታችን እንደሚያሳልፋ ይገባቃታል? ያውቃሉ? ይህንስ በምተዋል? ለዚህስ ምንይላሉ? አለ

ቦሬያም አይንዋን አፍጣ ተቆጥታ ብዱን ከአሉች በኋላ ወንበሩዋ ላይ በመንቆራጠጥ ትንሽ አሬስዋን ነቅንቃ መለስ ብላ በመቀመጥ ለመሆኑ ምንድነው የአሉት? ይገርማል እኮ ምንድን ነው የአሉት?...ተረጋግታ ዱምጹዋን ዝቅ አድርጋ "አባኮያትን እንዳው አደራ እንደዚህ ዓይነቱን የሚዘገንን የሚቀፍ ለጆሮ ደስ የማይል የሐሰት ወሬ ስለአገሬችን ከማስፋፋት ቆጠብ ይበሉ:: ይህን አመከርያታለሁ::ሌላው ቢቀር ስለውዱ አገሬችን ለኢጣሊያን ብለው ከእንዲህ አይነቱ አነጋገር ጠንቀቅ ይበሉ::በአገሬችን በኢጣሊያን ስም አማንዎታለሁ::ብላ በመስመአበ ወልዱ መንፈስ ቅዱስ በማለት ፋትዋና ደረትዋ ላይ መስቀል ባለች::

በቅርቡ እንደተከታተልነው ከዚህ ጋዜጣዊ መግለጫ ወዲህ በዙ የፊልም ተቀንያኖች የቢኖሬ ሉሬን አሳዛኝ ሁኔታ ተካፋይ በመሆን ተቃውሞአቸውን እንደአሰሙና የአገር ውስጥ ገቢ ከስም በበጊ ማስረኛ በኢጣሊያን ቴሌቪዥንና በጋዜጣ ላይ አዘጋጅ ጋዜጠኞች ትክክለኛውን ሥዕል ለህዝብ እንዲያቀርቡ አቤቱታቸውን ስልክ አየደወሉ እንዳስታወቁ ይታወቃል:: በተጨማሪም አያሌ ፍቶገራፍ አንሺዎች፣ሲኒማ አዘጋጆችና አቀናባሪዎች፣ጋዜጠኞችና ቃል አቀባዮች ባይሰክ ዝሬናገፍ የቀረው በሬ.ስ የራስን ህይወት የማጥፋት መከራዋና የአሥር ቤት መከራ ዘመንዋ የችግር ዋ የመንፈስ ተካፋዮች በመሆን ከጉንዋ እንደሚቆሙ በቴሌግራም፣በደብዳቤና በስልክ ገልጸውልታል::ተአምር በየቤቱ::ገሩም ነው ሻል::የወይዘሮ ቦሬያ ሉሬን የአሥር ቤት ሁኔታ እንደዚህ ሆና ባለ በሌላ በኩል ከዚህ በፊት ስምተነው የነበረው አሁንም የምንሰማው በዚህ ዓለም ላይ የአሉት አሥር ቤት ሁኔታዎች በእርግጥም አሳዛኝና ቸው::ሁኔታቸው የሚዘገንና የሚያስቀቅ ነው::

በዚህ ዓለም ላይ የአሉት አሥር ቤቶች ከመንግሥት መንግሥት ከቦታ ቦታ ከህብረተሰብ ሥርአት ሥርአትየተለያዩ ናቸው:: አንዱን መንግሥት ከብዙ ገጽታዎች በመመርመር ይህ መንግሥት ምን እንደሆንለመግለጽ ይቻላል::እንደኛው እሥረኞችን በሚመለከተው ነው:: በአንዱ መንግሥት ሥር የአሉት የአሥረኞች ቁጥር፣የአሥረኛ መብት፣ የአሥር ቤቶ ሁኔታ፣ አስተዳደር፣ የበበአዊ መብት መከበር፣የአገሬቶ ህገ ይህም ህገ የሚፈቀደው፣ የሚገልጸው መብቶች፣ጠበቃ፣ ሕክም፣ምግብ፣መጽሐፍት ቤት፣ መዝናኛ፣ ሥራ የሥራ አይነት፣...ወዘተ...ወዘተ በሥልጣን ላይ የአለው መንግሥት ምን እንደሆነ በአጠቃላይና ገጽታውን ሊጠቀመን ይችላል::

የታሪክ መጽሐፍትን ስናገላብጥ፣ አሥረኞች የነበሩበት ሁኔታ ዛሬም ያሉበት ሁኔታ ፍጹም የሚዘገንን ነው :: ከድንገኛ መቍጥ፣ለአራዊት ምግብ ከመሆን፣ከሰውነት አካል መጉደል፣ መገረፍ፣መሰቃየት፣... እስከ ዘመናዊ እሥር ቤት ድረስ ያለው በሙሉ የሰው ልጅ ጭካኔንና አረመኔያዊነትን የሚያሳይ ነው::

የቬቶች አሥረኞች ሁኔታ ሌላው ቢቀር በቬትናም ጦርነት ያየነው ከብረት በተሠራ ቅርጫት ውስጥ እንደ ወፍ እየተያዙ ምግባቸውን የምግባቸውን ትራፊ እዚያው ውስጥ፣አይነምድራቸውን እዚያው ውስጥ፣የወር አበባቸውን እዚያው ውስጥ የአልደረቀ ቁስላቸውን እዚያው ውስጥ፣ ከአለመታጠቢያ እዚያው ውስጥ እንደ ቆማ እንደከረሩ፣ እንደበሰበሱ ይደረግ ነበር::ይህ ሁኔታ ከቀረ አሥርም አመት አልሆነውም::በባንኛ፣በስደፍ፣በዱላ፣በብረት፣በአባት፣በሞቀ ውሃ፣በፈላ ዘይት ብልታቸውን የተጠበሱና በዚህም ምክንያት አካለ ስንኩል የሆኑ የአእምሮ መናወጽ የደረሰባቸው በቀላሉ የሚቆጠሩ አይደሉም::ይህም በሰባ አመተ ምህረት ውስጥ ይሰማ የነበረው ሁኔታ ነው:: የአሜሪካኖች ሥራ::

በሶቭየት ህብረት፣በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች በኢትዮጵያ ቢተረጎም "ዓማኡሌል ዕብዶች ህክም ቤት" የሚባለው ጉረኖ ውስጥ የሚወረወሩት፣በከባድ የጉልበት ሥራዎች ልባቸው የሚጠረው ፣በመድሐኒት መርፌዎች አእምሮአቸውን የሚስቱ፣ከዚያም በላይ በበሽታ የሚሰቃዩ የሰው ልጆች ቁጥር አይጠል ነው:: ሰው በሰው ላይ ሲጨክን/ አቤት አቤት አውሬም እንደዚህ አይሆንም::

<u>ምሳሌ ቁጥር አንድ</u>:: የጀርመን ፋሺስቶች ከአለማደንዘዣ ነፍሰ ጡር ሴት ሆድ ዕቃ እየቀደዱ የአልተወለደ ልጅ ህይወት በስሳ ካራ እየተለተሉ አያሌ መከራ ያደርጉ ነበር::

<u>ምሳሌ ቁጥር ሁለት</u>::የዲሞክራሲን ይዘት ቀንጠት ያህል የማያውቁና የማይረዱ የአንአባበለው፣ገደለው፣አሠረው ፖለቲካ የሚያራምዱ ጭፍን አረመኔ መንግሥታት የሰው ልጅ ህይወትን ለመቀጣጫ፣ለማስፈራሪያ በአነቡጣ አስተባበብ"ለማስተማሪያ"በያለበት የሚረሸኑ ናቸው::በአንዱ አሥር ቤት ውስጥ የአሥረኛው ቁጥር ከፍ ከአለ የጥፋቱ ዓይነት ይለያይ አይለያይ፣ ጥፋትም አይኑር፣አንዱ ልዩ ሁኔታ ይፈጠር፣አንበል ወደጦር ሜዳ የሚላኩ ወታደሮች ያጉረምርሙ ከአቅራቢያው አሥር ቤት በካሚዮን መቶ ሁለት መቶ አሥረኞች እንደበግ ተጭነው በየጦር ሠፈሩ የወታደር ልብስ ለብሰው እንደከፍተኛ ወታደር በተሰለፈ ጦር ፊት ከተደረደሩ በኋላ በአስፈሪ ደስኩር እንዲረሸኑ ይደረጋል::

ጆሮ የአለው ሰው ብዙ አሰብአዊ ድርጊቶችን ከየአለበት ይሰማል::አይን ያለው እንደዚሁ አያሌ አሰቃቂ ድርጊቶችን ያያል::እሳይ እንዳልነው የአንዱ መ



ንግሥት ዲሞክራት መሆኑና አለመሆኑ አንደኛው መለኪያ ስንት ሺህ ሰዎች በእሥር ቤት አፍና እንደያዘ ቢጠየቅ ነው::አሥረኞችም በእንዴት ያለ ሁኔታ ቢቀረሩ ነው::እንደእሥር ቤት መጥፎ ነገር የለም::ከሰማይ በታች ያለ ሲኦል ማለት ነው::የሥኘራ ሱሬንም አሥራት ትቀልዓሳችሁ::ወይ ባትሉንና በደንብ ብታስቡ እንደዚሁ ቢያንስ ለአሷ መጥፎ ነው::

በአገራችን የእሥረኛ ቁጥር እልፍ እልፍ ዝቅ ቢል እንዳንዴም እንደአፈ ጠባይ በገፍ እንደሚጨምር የዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶች በየጊዜው ይናገራሉ::እስከምናውቀው ከ30 ሺህ እስከ 40 ሺህ የሚጠጉ በወታደሩ የአምባገነን መንግሥት እሥር ቤት ተወርውረው ይገኛሉ::ከነዚህም ውስጥ ወደሰባት መቶ አሥረኞች እንደተፈቱ በአለም አቀፍ የዜና ወኪሎች ተገልጿል:: ታዲያ ከዚያ ሁሉ አሥረኞች ምንአለበት ትንሽ ብትጨምሩ ቶሎ ? አንዱ አሥር ሺህ::አንዱ ሃያ ሺህ ያህሉን::ሁሉንም::

-//- -//- -//-

<u>የዓለም ጋዜጦች ስለኢትዮጵያ ምን ይላሉ</u>??

በጥቅምት ወር 1982 የወጣው ኒው አፍሪካ መጽሔት በእትሙ ውስጥ የሚከተለውን አስፍሯል:: " በኤርትራ ላይ የስድስተኛውን ጦር ዘመቻ ሁለተኛ ክፍል፣ በምሥራቅ ጀርመኖች፣በሶቭየቶች፣ በኩባውያን በሚሰለጥነው የአየር ወለድ ክፍል ለመጀመር የወታደሩ መንግሥት ዕቅዱ አውጥቷል::ይህ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ፣ማለትም ዝናሙ ቀለል በሚልበት ጊዜ የሚከፈተው ጦርነት አጠቃላይ ይዘታ እንደሚኖረውና በተለይም በናቅፋ ላይ እንደሚያተኩር ይነገራል::ከከርቱም በሚደርሱት የወታደር ዜናዎች መሠረት፣ የአየር ወለዱ ክፍል በኩባውያን መኮንኖች እንደሚመራ ይነገራል::ይህም በቅርብ ጊዜ ወዲህ ሶቭየቶች በአዲስ አበባ፣ በአሥመራና በሰሜን ምሥራቅ ኤርትራ የወታደሩን የበላይ አመራር ከመረከባቸው ጋር የተያያዘ ነው::

በአንዱ በኩል በአዲስ አበባ የፀጥታ ክፍል እንደተገኘውና በሌላ በኩል ደግሞ ከምርኮኞችና ከዲፕሎማቶች አካባቢ እንደተረጋገጠው ፣ ፊልድ ማርሻል ዲሚትሮቭ የተባለው ሩሲያዊ በኤርትራ ነፃ አውጭዎች ላይ ለሚደረገው ጦርነት ስልትና አካሄድ ሙሉ ኃላፊነቱን ወስዷል::በመሆኑም ሊቀመንበር መንግሥቱ በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ይዘት የነበረውን የጠቅላይ ጦር አዛዥነቱን ሥልጣን እንደለቀ ሆኗል::ከዚህም በላይ ሁለት የሶቭየት ጄኔራሎች ከ200 የጦር አማካሪያ

ች ጋር በቀጥታ ጦርነትን እንደሚመሩና በጠቅላላውም በግምት 2000 የሚ ደርሱ ሩስያውያን በጦር አማካሪነት እንደሚያገለግሉ ይነገራል"።።

አንባቢ ይህ የወታደሩ መንግሥት የዉጭ ዱንበር ፖሊሲና ህዝብ ጥፍዉ ሩ እንደሁም ቦሸየቶች በተባባሪነት በዚያውም የጦር መሣሪያቸውን መፈተሻ ማዱ ረጊያ፣ም ን ያህል አገራችንን ወደባስ መቀመቅ ውስጥ እንደሚከቷት ባትገነዘብ አትቀርም።።ይህ ህዝቦችን ማለቂያ እንዲደረግ በየጊዜው የሚደገሰው ጦርነት ሊ ቆም የሚችለው የወታደሩ አምባገነን መንግሥትና ገብረአበሮቹ በህዝባዊ አመጽ ዲመሰሱ ብቻ ነው።

-//- -//-

ፍራንክፈርተር ሩንድሻው በ26.10.1982 ባወጣው እትሙ የሚከተለው ን አስፍሯል።።"ሮይተር እንዳወራው፣ ባሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ አሥራ አራት ክፍለ ሀገሮች ውስጥ በአሥራ ቦስቱ ላይ ድርቅ ደርሷል።።ይህ ንንም ምክንያት በማድረግ የመልቦ ማቋቋሚያ ኮሚሽን ተጠሪ የሆነው ሻለቃ ታሥፋዬ በርሃኑ ለውጭ ሀገር እ ርዳታ ሰጭዎች አቤቱታ አቅርቧል።።በተጠሪው ግምት፣ ድርቁን ለመወጣት ከ400000 እስከ 500000 ቶን እህል እንደሚያስፈልግ አስታውቋል።።ከዚሁም ውስጥ በአውሮ ፖ የጋራ ገበያ ሀገሮች የ 150 000 ቶን እህል እርዳታ እንዲያደርጉ ተጠይቀዋ ል"። ድርቀትና ጦርነት ርሃብና ችግር፣ ምንአልባት ሁለተኛው የቷ ትት?

-//- -//-

በ27.10.1982 የታተመው"ታገስ ስፒገል" የተባለው የምዕራብ ጀርመን ጋዜጣ የፖለቲካ እሥረኞችን በሚመለከተው አምነስቲ ኢንተርናሽናልን በመመርኮዝ የ ሚከተለውን አስቀምጧል።።"አምነስቲ ኢንተርናሽናል በ1981 መጨረሻ ባቀረበው ዓ መታዊ ሪፖርት ላይ፣ በ121 ሀገሮች ውስጥ ሰብዐዊ መብት እንደተደፈረ በማመልከት በብዙ አፍሪካ ሀገሮች፣ሰዎች ካለምንም ፍርዱ እሥር ቤት ውስጥ እንደሚታጐሩ ይ ገልጽና በተለይም በኢትዮጵያ፣ በደቡብ አፍሪቃ፣ በኡጋንዳና በዛዪር ላይ በፖለቲካ እሥረኞች ላይ በዙ ጭካኔና ግፍ እንደሚደርስ ሪፖርቱ ማመልከቱን ያብያል"።

ተጨማሪ ዜና ገጽ 9 ላይ ተመልከት።።



## ነፃ አምድ

### ኪነት

ታዲያስ መንደሬ ?
አክበቴ የተቀበረብሽ
የተወለጸሁብሽ ያደግሁብሽ
ጭቃ ያቦካሁብሽ

ታዲያስ መንደሬ ?
ከእናቴ ሆዱ ወጥጨ
እምብርቴ ዘልዩ ፈንጥቼ
በጣቶቼ ጭቃ ቧጥጨ
ነፍስ የዘራሁብሽ በርትቼ

ታዲያስ መንደሬ?
ያደግሁብሽ ጉምበስ ቀና ያልኩብሽ
መነባት ቢያቀተኝ ያለቀስኩብሽ
በጨቅቴ ያስታጋባሁብሽ

ታዲያስ መንደሬ ?

በአንቀልባ የታዘልኩብሽ
ወገቤ በአብሽ የታሸብሽ
ስሞህ አሸሩሩ የተባልኩብሽ

ታዲያስ መንደሬ ?
ከውጭ ሆኜ ባስታውስሽ
የትአየለሌ ሆኜ ስናፍቅሽ
የማረብሽ የማልዘነጋሽ
በየጊዜው የማስቻውስሽ

ታዲያስ መንደሬ ?
ከመንደር መንደር ወስደው
ወያያና ወዴህ ብለው
ተቀባበለው አባዱገው

ታዲያስ መንደሬ ?
አባህር ማዶ መጥቼ
ስንትና ስንት አገር አቋርጨ
ከሩቅ እንዓላይሽ ተጋርጬ

ታዲያስ መንደሬ ?
ጉምበስ ቀና ያልኩብሽ
ቀስ በቀስ ያደግሁብሽ
ፊደል ሀዋሪያ የቆጠርኩብሽ

ታዲያስ መንደሬ ?
ፊደል አልገባ ቢለኝ የተኮረኮምኩብሽ
ምርር ብዩ ያለቀስኩብሽ
በለበቅ ... የተገረፍኩብሽ



ታዲያስ መንደሬ ?
ፈረንጅ አገር መጥቼ
እንዳረባሽ ብዬ ፈርቼ
አስሳስልሻለሁ በርትቼ

ታዲያስ መንደሬ ?
ይኸውልሽ ዘመን አለፈኝ
ካንቺ ከተቆራረጥኩኝ
ጠነኘ አይደለም የቆረጥኩኝ

ታዲያስ መንደሬ ?
ሬዲል ሃጥሪያን ቼጥሬ
አቡጊዳን አምበልብዬ
ዓቂትን ደገሜ ደጋገሜ
ስጨርስ መሠረተ ትምህርት ገብቼ

ታዲያስ መንደሬ ?
አጠፋሪስ ቀጥሬ
አሽሽቼ በእጄ
የተጫወትኩብሽ በአገሬ

ታዲያስ መንደሬ ?
አሉሆይ አሳሉሆይ ያልኩብሽ
ዱብብቆሽ የተጫወትኩብሽ
በየቀሻው ስር የተፈፈቅኩብሽ
እንደቀኛ ደቢሩ ቀኘኩብሽ


ታዲያስ መንደሬ ?
ፈረንጅ አገር መጥቼ
ከፍተኛ ትምህርት አፈልጋለሁ ብዬ
ወዲያና ወዲያና ወዲህ ተንከራትቼ
መያዣና መጠበቂውን አጥቼ

ታዲያስ መንደሬ ?
የጨርቅ ኳስ በፍቼ
አንዱ ሁለት ብዬ ተጫውቼ
ጥየሽ የመጣሁት ተነስቼ

ታዲያስ መንደሬ ?
ዱርሱህ ንቤ ያልኩብሽ
ጠጠር የተጫወትኩብሽ
ቢዬ ያዱበለበልኩሽም
ዝሄየን ደስብሶኝ ኳባለፍኩብሽ

ታዲያስ መንደሬ ?
አባህር ማዶ መጥቼ
የማላውቀው አገር ተበድጄ
ትምህርት አገኛለሁ ብዬ ተፈጨጨ
ፍዳ ገብቼ ተበባዬቼ
ስንትና ስንት መከራ አይቼ

ታዲያስ መንደሬ ?
የማያልፍ ነገር የለምና





ቢያልፍ ያለፉልና
ትምህርት አገኘሁና
ተባዝልኝ ያሰብኩት ሆነና

ታዲያስ መንደሬ ?
ባላ ስርቼ ያነጣጠርኩብሽ
ከዛፍ ላይ ወፍ የጣልኩብሽ
አዱን ላቀመ አጸም የደረስኩብሽ

ታዲያስ መንደሬ ?
ገርምሼ አደገ አደገ ብዬ
እንገጫ ላናቀል ወንዝ ዓር ወርጄ
አበባ አየሁኝ ቢሉ አብሬ አወርጄ

ታዲያስ መንደሬ ?
ትምህርት ቤት ገባሁና
መልፍ እያገላበጥኩ ስዘናና
ማርኩሁም የሚባል ነገር አየሁና
ወዲያና ወዲህ አወረዱኝ

ታዲያስ መንደሬ ?
ገሬ ተጋብቼ አልገባ ብሎኝ
የሰው ልጅ ታሪክ የመደብ ትግል ቢለኝ
አውቆቼ አውርጄ አስባስልኩኝ
እንዴት የሰው ልጅ ከመደብ ጋር ይታገላል
አልኩኝ

ታዲያስ መንደሬ ?
ዓመሬ ቆርጠዉሆ ብዬ
ችቦ ለቆሜ አቀጣጥዬ
የጨፈርኩብሽ ያልኩብሽ ሆያሆዬ

ታዲያስ መንደሬ ?
አበባ ሰሌቼ በየመንደሩ ሄጄ
እንቁጣጣሽ አደረስዎት ብዬ ሰግጄ
ትሎ ሰጡኝ አጅ ነስቼ

ታዲያስ መንደሬ ?
የመደብ ትግልም ገባኝና
ፍልሚያ መገጠም ያስፈልጋል አሉኩኝና
ክርክር ገጠምኩኝ ከሰው ጋር ሆኜና

ታዲያስ መንደሬ ?
ከዚያማ አውቄ
ሊቃ ሆኜ ተመራመሬ
አበየት በቻ ብዬ አምርሬ
መደረግ አለበት ብዬ አክርሬ
ያስፈልጋታል አልኩኝ ለሀገሬ

ይ ቀ ጥ ላ ል



## የኢኮኖሚ እድገትና አካባቢ በካፒታሊዝም፡፡

አንዱን እንቁራሪት በዱግ አድርገህ የፈላ ውሃ ውስጥ ብትወረውረው አይጣል ነውና በአለ በሌለ ኃይሉ ከዚያ መዓት ለማምለጥ መጣሩ አይቀርም፡፡እንዲህ ግዜ/ እንቁራሪት በአንዴ ተወርውሮ መሬት ላይ ዱብ ይላል ?

ሌላ– በትንሹ ቀስ እያለ አባት በሚሞቀው ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ብታስቀምጠው ግን ያ ተስፈንጣሪ እንቁራሪት ለረዥም ጊዜ ወዲህ ወዲያ ባይወራጭ ምናምኒትም እንቅስቃሴ ባያሳይ ሙቀቱ ብሎ አስከሚፈረርስ ድረስ እዚያው ውሃ ውስጥ ይቀቀላል፡

በምርምር ጣቢያ ውስጥ የማይሞከር ተዓምር የለም፡፡ብዙ ይቻላል፡፡ችግሩ ይህ አይደለም፡፡ችግሩ ፤ ችግሩ አሳሳቢ እንደ ፤ ጉዱ ፤ ጉዱ ታዲያ የዚህች የእንቁራሪት ምሳሌ አለምንም ማጋነን ቁርጥ ያለ ዛሬ የአለንበት፤ የሰለጠነ ህዝብ አኗኗርና ሁኔታን በግልጽ ማሳየቱ ነው፡፡በአውሮፓ፤በአሜሪካና እንዲሁም በአንዳንዱ ትላልቅ የሶስተኛው ዓለም ከተሞች የሚኖሩት ህዝቦች ቀን በቀን፤ሰዓት በሰዓት፤ደቂቃ በደቂቃ በተመረዘው፤በተበላሸው አካባቢያቸው ውስጥ ቀስ በቀስ "ሙቀ" እያሉ "እየተፈረከከሱ" እንዳንዶቹም "እያረሩ" "እያለቁ" ናቸው፡፡

የካፒታሊዝም ሥርዓት መጥፎ ጎን ያውም አንደኛው መጥፎ ጎን ይሏችል፡ይህ ነው፡፡በመጀመሪያ ግን የካፒታሊዝምን "ጥሩ ጎን" እንዴያው ለታሪክ መለስ ብለን እንመልከተው፡፡ብዙ ህይወት እንዳየና እንደሚያውም እንደገና ሽማግሌ ለመናገር ቢፈቀድልኝ ይህቺ ገና ብቅ ብቅ ስትል በኋላም ወደተደላደለ ሥርዓት ተቀይራ፤ቀደመው የአለፉት እናቶቻችንና አባቶቻችን፤የሰው ልጆች በሙሉ ሊገምቱትና ሊያስቡት የአልቻሉትን እጅግ ብዙ ጉዶችን ይዛልን መጣች፡፡በአጭር ጊዜ ውስጥ የዚህችን ምድር መልክ በእሩጣን ቀይራለች፡፡

መቼም በፈረንሳይ የተነሳው፤ በጀርመን ብቅ ያለው፤በእንግሊዝ ገምባር ቀደም የነበረው፤በደች በንግድ የተራቀቀው፤በአሜሪካን "ሁሉን ነገር ያለ ገደብ የሚቻልበት" ብሎ የሚለፈለፈው፤ በአፍሪካ፤በእሲያ፤በደቡብ አሜሪካ በዱግ ቡል እየተክረከመ ቆርቆዞ የቀረው፤ በመጨረሻም የባእዶች አቀባባይ የሆነው...ይህ ሁሉ ፍጡር በየመልኩና በየፈናው የተጓዘው ጎዳና እንደየራሱ ነው፡፡እያንዳንዱን መዘርዘሩ ነገሩን ስለሚያረዝመው እዚህ ላይ እናብቃና ወደ ፍሬ ነገሩ እናተኩር፡፡

ሆኖም በአጠቃላይ፡– የሰው ልጅ ከአለፉት ሁለት መቶ ዓመታት ወዲህ ያደረገው እርምጃ በታሪክ ውስጥ በጣም ፈጣን ነው ብል አልተሳሳትኩም፡፡በተለይም በምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ካፒታሊዝም ብቅ ከአለ ጀምሮ፤ የኢንዱስትሪ አብዮት ከተካሄደ በኋላ የሰው ልጅ የሥራ እድገቶች እጅግ በጣም ፈጣን ሆነ፡፡የምርት መሣሪያዎች በተፋጠነ መንገድ በተፈጠሩና በተቀያየሩ ቁጥር የአካባቢው ሁኔታ የግዱ እንዲለወጥ ሆኖአል፡፡



የከተሞች መቆርቆርና መስፋፋት፤ ትላልቅ ቤቶችና በማይ ጠቀስ ፎቅ ቤቶች እንዱ ላይ ተደራርቦ መሠራት፤ በዚያው መጠን የከተማው ህዝብ ቁጥር መጨመር፤የሆስፒታሎች፤ የትምህርት ቤቶች ፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፤ቡና ቤቶች፤ ሆቴል ቤቶች፤የንግድ መደብሮች... ወዘተ ...ወዘተ፤ በሰፊው መስፋፋት ከቀድሞ ኢንዱስትሪ አብዮት የነበረውን ሁኔታ ልዩ መልክ ሰጥቶታል፡፡በዚያው መጠን መንደርን ከከተማ፤ ከተማን ከከተማ፤ ሀገርን ከሀገር የሚያገናኙ የአየርና የባህር መንገዶች፤ የባቡርና የመኪና መንገዶች በሰፊው ተስፋፍተዋል፡፡ይህም በሰዎች፤በከተሞች፤በሀገሮች መሀከል የንግድ ግኑኝነትን የኢንፎርሜሽን መለዋወጥንና መስፋፋትን በተፋጠነ መልክ እንዲያድግ አድርጓል፡፡የሰው ልጅ ወደ ፊት በተራመደ ቁጥር አዲስ የታሪክ ምእራፍ ውስጥ እየገባ፤በቴክኖሎጂ እየተራቀቀ ተፈጥሮን እየተቆጣጠረና በዚያው መጠን ተፈጥሮን እያበላሸ ቢሄድ በቀላሉ ሊወጣው የማይችለው ውስብስብ ችግር ውስጥ እንደወደቀ ሆኖአል፡፡

አንዱ ወረሰት የሌለበት ካፒታሊዝም ለሰው ልጅ የአመጣው "ነፃነት" ቢኖር ከባላባት መቴ ጋር እንደእንስሳ ተሰማርቶ በጨዋነት የሚተዳደረውን ገበሬ "ነፃ" አውጥቶ ወደ ተንቀሳቃሽ የጉልበትን ዋጋ ሽያጭ ወዝ አደር እንዲሆን ማድረጉ ነው፡፡ይኸውም ካፒታሊዝም ለቴክኒክ፤ለሳይንስ፤ለምርምር በር መክፈቱና ከፊውዓሊዝም ጋር መጋፈጡ፤ፊውዓሊዝምን እንደየአገሩ በተለያየ መንገዶች እንኮታኮቶ መቀጣጡ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ይኸኛው ገበገቡ ግን ፈጽሞ ብቻውን አይደለምና ጠቀሳሳውን ሙገባ ለካፒታሊዝም ብቻ መስጠቱ ተገቢ አይደለም እላለሁ፡፡

ወደ ተነሳንበት እንመለስና፡– ለመሆኑ ካፒታሊዝም ምን ዓይነት የአካባቢ ጠጣ ውስጥ ነው ያለው? ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ፤የኢንዱስትሪዎች በየቦታው መስፋፋት ትላልቅ ከተሞችን መልክና ቅርጽ ፍጹም ቀየረው፡፡የኢንዱስትሪዎች መዶዶ መስፋፋትና በቴክኖሎጂም መሻሻል በእርግጥ የኢንዱስትሪ ምርቶች በጥራትም ሆነ በብዛት ከማሻሻል፤ከማባደግ አልፎ የወዝአደሩን ጉልበት ዋጋ እስከተወሰነ ቢቀንሰውም የኢንዱስትሪ መስፋፋት አካባቢውን በሚተፋት የተቃጠለ መርዝ እንዲበላሽም አድርጎታል፡፡

የረዣዥምና ትላልቅ ፎቅ ቤቶች መሠራት፤የመኪና ጋዝና የኢንዱስትሪ ጭስ በአጸዋትና በአንስሳ እንዲሁም በሰው ላይ ከፋኛን ሁኔታን አስከትሎአል፡፡ይህ ሁኔታ የተፈጥሮን የአየር ለውጥ ከመቀነሱም አልፎ አየር እንደልብ እንዳይንቀሳቀስ አግዶታል፡፡የሰዎችን የእርስ በእርስ ግኑኝነት ነሳዊና ጠባብ የሚያደርገው የዚ ሁኔታ በሰዎች ላይ የአእምሮ መታወክን፤የመንፈስ መሸበርን የመሳሰሉ የዘመናዊ ትላልቅ ከተማ ነዋሪዎችን በሽታ ወለደ፡፡የልብ ድካም፤ጭንቀት፤ነቀርሳ በሽታ፤በዝሙ የሆኑ

ልጆች መወለዱ ፣... ወዘተ. ከዚህ ጋር ተያይዘው የመጡ ናቸው፡፡

ይህንና ይህን የመሳሰሉት ዘመናዊ ችግሮችን በደንብ እንዲገመለከተው ከ አለታቹ የኑሮ ሁኔታ እንጀምር፡፡

በጨንነት ይመገቡ፤ይኑ፤አይዲፃ እንደማትባሳ ይርዛም የሚሉ የነገዱ ምል ከተችን ምክር ብንወስዱ፣ ወይም የግል ልኪማችን የሚስጠን ምክር በደንብ በናባ ምጥው ወይም የምግብ አተያየልን ዘዴ የጥያስተምርን የማዉቤት መጽሐፍ እንደያው እንደአጋጣሚ ዘርጋ አዩርገን በንመለከተው ቁርስ መበሳት ለአለት የሰውነት ጉል በት ማከማቸት ጠቃሚ ነው፡ይለናል፡ ቁርስ አንዱ በርጩቶ ወተት፤አንዱ እንቁላል፣ አስከ አራት ቁራጭ ነጭ ወይም ጥቁር ዳቦ፣ ሁለት የሻይ ማንኪያ ቅቤ፣ ስኳር፣ማር ወይም ማልመራዲ ...ወዘተ ይወስዱ ይላል፡

ቤትም ሆነ ትምህርት ቤት ቁርሱን የሚቆርስ ተማሪ ከዚህ ውስጥ የተጠቀሱትን ቢያገስ አንዱ ሁለቱን ኪአለበለዚያም ለምሣ ወይም ለአራት የማመገባቸው ናቸው ፡፡ አስቲ ከጠቀስናቸው ውስጥ አንዱን ወስደን እናውባ፡፡በርጭቶ ወተት፡- ወተት በአው ሮፓና በአሜሪካ በገፍ የሚመረት ነው፡፡አብዛኛውን ጊዜ የወተቱ ዋጋ ከወተት በዛት የተነሳ እንዳይወዱቅ፣ ዘቀ እንዳይል አየተባለ የተሸጠው ተሸጦ የአልተሸጠውም ለሌ ሳ የወተት ምግብ ዓይነቶች መሥሪያ ውሶ፣የተቀረው የወተት ጋን እንደሚደፋ ሁላችሁ ም ባትሰሙ አትቀሩም፡፡መከከለኛ ወተ' የምትሰጠው የአውሮፓ ላም በቀን 20 ሊትር ወተተ ትተለስለች ፡፡ አሥር፣ ሃያ፣ሃምሣ፣ ወዘተ . ጥገቶች ያለው ገበሬ ጥዋት ተነስቶ አነዚህን ሁሉ ላሞች ለማለብ አይችልም፡፡ ላሞችየሚታለቡት በማከና ይሆናል፡፡

በመኪና የሚታለቡ ላሞች ደገም በቅርቡ የወጣው ምርምር ጥናት እንደሚያስረ ው በጤና በኩል በአጅ ከሚታለቡት ላሞች ንጽህ ስሆኑ— ወተቱ በቀላሉ በጀርሞችና በባክቴሪያዎች የማመረዝ ነው— በሌላ በኩል አጸያፊና ለወተት ወዳጆች ቀፋፊ የሆነ በመገልና በደም በብዛት የተበላሸ እንደሆነ ጠቁሞዋል፡፡ይህንንም ቢዘከዝኩ እንደዚ ሀ ይላሉ፡

ጥጃው በምላሱ ጡትን ከመንጋጋው ጋር አስጠግቶ እንደሚያሸውና ወተትን እንደ ሚገነጠው፣ በአጅም ላሚቷ ስትታለ ል በእንደዚያው ዓይነት ነው፡፡ ይህም ማለ ት ጥጃው ጡቶችን ተራ በተራ ቢጠባ በአጅ ግን ሁለት ጡቶች ተራ በተራ ይታለባሉ ፡፡ በመኪና የሆነ እንደሆነ ግን መኪናው አራቱን ጡቶች በአንዴ ይጉርባል፡፡ከአራቱም በአ ንዴ ወተቱን ይመጣል፡፡ጡቶቹም የተለያዩ ስለሆኑ አንደኛው ጡት ውስጥ ያለው ወተት ከሌላው ቀድሞ ስለሚያልቅ ፣ መኪናው የአለቀውን የጡት ጫፍ ከሌላው የጡት ጫፍ መለየ ት ስለማይችል ከአለውም ከሌለውም ጡት ጫፍ ወተት መጠጡን ይቀጥላል፡፡ በተለይ በአ ለቀው ጡት ጫፍ ላይ የሚጋመጠውን ውጤት እንመልከት፡፡



ባዶ ወተት የሌላው የጡት ጫፍ ከፍል በመኪናው ዝም ብሎ ስለመምጥ በወተት ፋንታ ወተት የለምና ደም ይተፋል ፡፡ ይህም በአንዱ በኩል ጡት ውስጥ ቁስል ስለሚፈጥር ሁለተኛም አየተደጋገመ በየቀኑ ስለሚደረግ ቁስሉ እየበሩ ፣ ጥቃቅን የደም ሥሮች በመኪናው ጉተታ አየተበጣጠሱ እንዲሄዱ ቁስሉም ለመድረቅ ባለመቻሉ መግል እንዲቋጥርና ከጊዜያዊ ቁስል ወደ ቋሚ እንዲሸጋገር ይሆናል ከዚህም በላይ አልፎ አልፎ ብቻ የሚመረመረው የወተት ማለቢያ መኪና ውስጥ በማ ንያ በመተው የተለያዩ ጉዱለቶች ያሉቸው ናቸው አንዳንዶቹ የአለታ ጉማ የሚሸከሙ የተባባተ ወተት መጉተቻ ትርታ የያዙበመሆናቸውም የላሞች ጡት እንዲቆስል ና መግልና ወተት እንዲተፉ ምክንያቶች ይሆናሉ ፡፡

በብዙ አገሮች በተደረገው ምርምር ከነማሽ በላይ የሚሆኑ የወተት ሰጪ ላሞች ጡት የቆሰሉ መሆናቸው ተደርበብታል ፡፡ ለዚህም የወተት ማለቢያ መኪናውን እንደመቀየር በሌላ ተስማሚ መሣሪያ እንደመተካት ብዙ አርቢዎች በአቡቲ የላሞችን ጡት አየወጉ ወተቱን አያበላሹ ነው ፡፡ መድሐኒቶችም [illegible] በዐሩቶ ምክንያትም የበሽታው መነሻ መኪናው በመሆኑና በየቀኑም ጡት ላይ [illegible] ባለመቀየሩ ነው ፡፡ ከዚህም የተነሳ በጡት ውስጥ የሚገኙ ባክተ [illegible] በአንቲባዮቲክ በቀላሉ የሚሞቱ አይደሉም ፡፡ / /

ይህን ሁሉ የሚያውቁ የወተት ተቀባይ ነጋዴዎች በጋተቱ ውስጥ ያለው መግልና ደም በሌላ ከተወሰነው ገደብ በላይ ከሆነ መክፈል ከሚገባቸው ከእያንዳንዱ ሊትር ሁለት ሳንቲም በቅጣት ይገዛሉ ፡፡ ይህንንም ወተት ከሌላው ዝቀተኛ መግልና ደም ካለው ወተት ወይም ከሌላ ወተት ጋር በመቀላቀል በሕግ ከተወሰነው ገደብ በታች በማው ረድ ገበያ ላይ ያወጡታል ፡፡

ዛሬ ግን አባቶቻችን የአባቶች ከወተት ማለቢያ መኪና ብቻ የሚመጣውን አደጋ ነው ፡፡ ለመሆኑ ላሚቷ ምን ዓይነት አደጋ አለባት ብላችሁ

[illegible]

ቀርሳችሁ የአነሳሳ ጉዞ ያታወ ፡፡ ቀርሶ አንበሳለን ፡፡

ይህንና ይህን የመሰሉትን ጥያቄዎች በሚቀጥለው መጽሔታችን ላይ እናወጣለን ፡፡